# በስኬቶች የታጀበ ቃል ኪዳን ልደት

ክፍል አንድ

ኢብሳ ነመራ 12-3-14

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ ሕገመንግስት ከፀደቀ አነሆ በመጪው ሰኞ ህዳር 29፣ 2007 ዓ/ም 20 ዓመት ሞላው። ይህ ህገመንግስቱ የፀደቀበት ሃያኛ ዓመት ዘንድሮ "በሕገመንግስታችን የደመቀ ኢትዮጵያዊነታችን ለህዳሴያችን" በሚል መሪ ሃሳብ ከሚለበረው 9ኛ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ጋር በአንድ ላይ ይከበራል። የዘንድሮ የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች 9ኛ በዓል በቤኒሻንጉጉን ጉምዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ ከተማ አሶሳ ነው የሚከበረው።

የኢፌዴሪ ህገመንግስት የፀደቀበንን ዕለት "የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን" በሚል ማክበር ለምን አስፈለገ? ጥያቄው በተደጋጋሚ ምላሽ የተሰጠበት አሮጌ ጥያቄ ቢሆንም ዕለቱን ለመዘከር ሲባል ማስታወሱ ተገቢ ነው የሚል እመነት አድሮብኛል። ለዚህ ጥያቄ ምላሽ መስጠት በግዜ ጎዳና ላይ ከሃያ ዐመታት በፊት ወደነበረው ሁኔታ ይወስደናል።

ኢትዮጵያ የተለያየ ቋነቋ፣ ባህልና ታሪክ ያላቸው የበርካታ በሄሮች ብሄረሰቦችና ሕዘቦች ሃገር ናት። የብሄር፣ ብሄረሰብና ህዝባቿ ቁጥር ከ80 በላይ  ነው። እንደው ለነገር መነሻ ይሁነኝ በዬ እንጂ ይህን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ አለ ብዬ አይደለም ይህን የጠቀስኩት። እነዚህ በሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በራሳቸው መልከዓምድራዊ ወሰን ውስጥ ዝንተ ዓለም ኖረዋል፤ በቋንቋቸው እየተናገሩ፣ ተፈጥሯዊና ማህበራዊ አካባቢያቸውን ለኑሮ በሚመች ሁኔታ የሚገሩበትና የሚመሩበት ስርአት አበጅተው፣ ይህም የምርትና የማህበራዊ ግንኙነት ባህላቸው ሆኖ፣ የገበያ ስርአት ኖሯቸው፣ መንፈሳዊ ፍላጎታቸውንም በእምነትና በአምልኮ ስርአት፣ በኪነጥበብ እያረኩ ነው ዝንተ ዓለም የኖሩት።

በሚኖሩብት አካባቢያቸው ላይ አካባቢውን አቅንቶ ከመኖር የመነጨ የባለቤትነት መብትም ነበራቸው። በአጠቃላይ የተለያዩ ብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዝቦች በዚህች ኢትዮጵያ ብምትባል ሃገር እንደ አንድ የራሱ ማንነት ያለው አካል (entity) ዝንተ ዓለም ኖረዋል፤ አሁንም አሉ።
የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የየራሳቸው ማንነተ ኖሯቸው እንደ አንድ አካል (entity) መኖራቸው ተጨባጭ እውነት ቢሆንም ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ በኋላ በሄራዊ ማንነትቻው እና የማንነተቸው መገለጫ የሆኑት ቋንቋ፣ ባህልና ወግ፣ ታሪክ . . . የህግ እውቅና ተነፍጎት ነበር። ይህን ያደረጉት መነሻቸው ከወደየሃገሪቱ ሰሜናዊ አቅጣጫ የሆነ በፈጣሪ የተሰየምን ነን የሚሉ የፊዉዳላዊ ዘውዳዊ ስርአት ነገስታት ነበሩ። ፊውዳላዊው የዘውድ ስርአት ተስፋፊዎቹ በሃይል አልፎ አልፎም ከየአካባቢው ፊውዳላዊ ነገስታትና የጦር አበጋዞች ጋር በጥቅም ግንኙነት በመተሳሰር ዲፕሎማሲያዊ ስልት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦችን በማስገበር ነበር ለማንነታቸውን ሕጋዊ እውቅና የነፈጉት።

በዘወዳዊው ስርአት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋቸው ህጋዊ እውቅና ተነፈጎታል። በቋንቋቸው ፍትህን ጨምሮ የመንግስት አገልግሎት ማግኘት አይችሉም ነበር። ፍርድ ቤት ቀርበው ጉዳያቸው ላይ ምንም በማይችሉት - በማይሰሙትና በማይናገሩት ቋንቋ እንዲሟገቱ ይገደዱ ነበር። ቋንቋቸው የትምህርት መስጫ ቋንቋ እንዳይሆን በህግ ተከልክሏል። ሕፃናተ አፍ ከፈቱበትና በብቸኝነት ከሚናገሩትና ከሚሰሙት ውጭ በሆነ ባዕድ ቋንቋ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እንዲከታተሉ ይገደዱ ነበር።

በዘመናት ማህበራዊና ተፈጥሯዊ አካባቢ እይታ (observation) እና ተሞክሮ የዳበረ የማህበራዊ ግንኙነት፣ የአመጋገብ፣ የህክምና፣ የአመራረት ስርአት፣ የሙዚቃና ዳንስ . . . ባህልና ወጎች እነደኋላ ቀርነት ተቆጥረው ያለመሰለጠን መገለጫ እንዲሆኑ ተደርጓል። እውነተኛ ታሪካቸው የፊውዳላዊ ዘውዳዊ ስርአቱን የበላይነትና ስልጡንነት ለማሳየት ተብሎ በተፈጠሩ ታሪኮች ተዛብቶ ነበር። እውነተኛ ታሪካቸው እንዳይፃፍ፣ እንዳይታወቅ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዳይተላለፍ ተደርጓል።

ከላይ በተገለፀው ስልታዊ አካሄድ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ብሄራዊ ማንነታቸው ርካሽና መናኛ እነደሆነ ተደርጎ እንዲወሰድ ተደርጓል። የብሄር በሄረሰብ አባላት ራሳቸው ያደጉበትን፣ የኖሩበትንና ማንነታቸው የተቀረፀበትን ባህልና ቋንቋ ትክክለኛነትና ትልቅነት ብጥርጣሬ እንዲያዩት፣ አልፎ አልፎም እንዲያፍሩበትና በሌሎች ፊት ማንነታቸውነ እንዲሸሽጉ፣ አንገታቸውን እንዲደፉ ያደረገበት ሁኔታ ነበረ። በቋንቋቸው የወጣላቸውን የመጠሪያ ስማቸውን የቀየሩ፣ ለልጆቻቸው በማያወቁት ቋነቋ ምንነቱን የማያወቁት መጠሪያ ስም ያወጡ የኢትዮጵያ ብሄሮቸ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች አባላት ምን ያህል እንደሆኑ አገር ይቁጠራቸው።

ሁሉም የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ዘውዳዊው ስርአት 'የእኔ ማንነት' ነው በሚለው በሄራዊ ማንነት - ቋነቋ፣ ባህልና ወግ፣ ሃይማኖት . . . ራሳቸውን እንዲቃኙ የሚያስገድድ ስትራቴጂ ስራ ላይ ውሎ ነበር። ይህ ስትራቴጂ ሁሉንም ብሄራዊ ማንነቶች ጨፍልቆ አንድ ብሄራዊ ማንነት ያለው ሃገር ለመፍጠር የተነደፈ ነበር። አንድን ብሄራዊ ማንነት ሆን ብሎ ማጥፋት በራሱ ተገቢ ያለሆነና ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ስትራቴጂው የተፈፀመበት ሂደት በተለየያዩ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ላይ አሸማቃቂ የስነልቦናና ቁሳዊ ጉዳት ያስከተለ እጅግ ፀያፊ ነበረ።

ይህ የሁሉንም የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዘቦችን ማንነት ጨፍለቆ የማጥፋት ስትራቴጂ ትንሽና ትልቅ፤ ዋናና ተከታይ ኢትዮጵያውያንን ሰይሞ ነበር። አንድ ብሄር ከሌሎች የላቀ ታሪክ ያለው፣ ሃገር መስራች፣ ተቆርቋሪ፣ ታማኝ . . . እነደሆነ ተደርጎ ሲወሰድ፣ ሌሎች በርካቶቸ ደገሞ ለሃገራቸው የማያስቡ፣ ሃገራቸውን አሳለፈው ሊሰጡ የሚችሉ ከሃዲዎች፣ . . . ተደርገው ይወሰዱ ነበር። እርግጥ ስርአቱ ሊፈጥረው የሚፈልገው ብሄራዊ ማንነት አባል የሆኑ ዜጎች፣ "ከስርአቱ ልዩ ጥቅም አግኝተዋል" እያልኩ እነዳልሆነ እንዲታወቅልኝ እፈልጋለሁ። በብሄራዊ ማንነታቸው የመሸማቅ አሰከፊ ሁኔታን ባይጋሩም እነደተቀሩት ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦቸ እጃቸው እግር እሰኪመስል አርሰው የሚኖሩ፣ የትምህርት እድል የሌላቸው፣ የጤና አገልግሎት የራቃቸው፣ መንገድ መብራት፣ ውሃና መሰል የመሰረተ ልማት ተጠቃሚዎች ያለሆኑ ያጡ የነጡ ደሃዎቸ ነበሩ።

እርግጥ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ብሄራዊ መብታቸውና ነፃነታቸው አለመከበሩ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ እንደሁለተኛ ዜጋ መታየታቸው፣ ለሚኖሩበት መሬትና በመሬቱ ላይ ላለ የተፈጠሮ ሃብት ወይም ወደብ ሲባል ብቻ ኢትዮጵያ የሚባለው ሀገር ውስጥ የተካተቱ መሆናቸው ቀዝቃዛ የኢትዮጵያዊነት ስሜት ሊፈጥርባቸው መቻሉ የሚያጠያይቅ አይደለም። ይህ የሆነው ግን ኢትዮጵያዊ ያለመሆን አብሯቸው የተፈጠረ ባህሪ ስላላቸው ሳይሆን ማንነታቸው እውቅና ተነፈጎት በመገፋታቸው ምክንያት ነው። ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦቸና ህዝቦች መሃከል የተዛባ ግንኙነት እንዲኖር አድርጓል፤ አነዱ ትልቅ ሌሎች ትንሽ፣ አንዱ ለሃገሩ ታማኝና ተቆርቋሪ ሌሎች የሃገረ ፍቅር ስሜት የሌላቸው ለባዕድ የሚያደሉ፣ በጥርጣሬ የሚታዩ ወዘተ አመለካከት ላይ የተመሰረተ የተዛባ ግንኙነት።

በዘውዳዊ ፊውዳል የነገስታት ስርአት በኢትዮጳያ ላይ የተጫነው ጭቆና ይህ ብቻ አልነበረም። ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ዘርማንዘራቸው የኖረበት መሬት ላይ የባለቤተነት መብት ተነፈጎቸዋል። በመሬቱ ላይ ለረጅም ዘመናት ከመኖረና ከመጠቀም የመነጨ የባለሃገረነት መብት ግነ ነበራቸው። ይሁን እንጂ ይህ መብት ተገፎ በገዛ ሃገራቸው ላይ መሬት አልባ እንዲሆኑ ተደርጓል።

የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ዘርማንዘራቸው ዝንተ ዓለም የኖረበት መሬት ላይ ያላቸው የመሬት ባለቤትነት መብት ተገፎ መሬታቸውን ገሚሱ ነገስታቱና መሳፍንቱ፣ የተቀረውን ደግሞ የስርአቱ የርእዮተ ዓለም (ideology) ክንፍ የነበረው ቤተ ክህነት ተቀራመቱት። ንጉሰነገሰቱና መሳፍንቱ ሕዝብ ሰፈሮ የሚኖረበትን መሬት አዲሰ አበባ ላይ ተቀምጠው ለመኳንነቱና ለቢሮክራት ተሻሚዎች በርስትና በጉልት ይሰጣሉ። ለባለውለታዎቻቸውና ለወዳጆቻቸው ይሸልማሉ። የህዝብን መሬት፣ ልክ እንደ አቡጀዲ እየሸነታተሩ ሁለት፣ አስር፣ ሰላሳ . . . ጋሻ መሬት እገመሱ ነበር የሚያድሉት፣ የሚሸልሙት።

ንጉሰ ነገስቱ፣ መሳፍንቱ፣ መኳንነቱና የስርአቱ ተሿሚዎች፣ የንጉሰነገስቱና የመሳፍንቱ ወዳጆችና ባለውለታዎች፣ እንዲሁም ቤተክህነት በዚህ አኳኋን የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ዘርማንዘራቸው ዝንተ ዓለም አያለሙ ይኖሩበት የነበረውን መሬት

ቀምተው የባለሃገርነት መብታቸውን ነፈጓቸው። የራሳቸውን መሬት እያለሙ ለባለርስትና ባለጉልት መሳፍንት፣ መኳንንትና ተሿሚዎች . . . ምርትና ጉልበታቸውን ለመገበረ ተገደዱ። በጭሰኝነት ለመኖር ከተገደዱበት ሁኔታ ውጭ የመኖር አማራጭ ስላልነበራቸው በገባርነት የተጫነባቸውን ጭቆና ተሸክመው ለመኖር ተገደዱ። በመሬታቸውና በጉለበታቸው ላይ የሚያዙት ባለርስትና ባለጉልት መሳፍንት፣ መኳንንት፣ ተሿሚዎችና ቤተክህነት ነበሩ።

ተዲያ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ሕዝቦች ይህን ስርአቱ የጫነባቸውን አስከፊ ፀያፍ ብሄራዊ ጭቆናና በዚህ ብሄራዊ ጨቆና ላይ የተመሰረተውን ለገባርነት የዳረጋቸን ኢኮኖሚያዊ ጭቆና አሜን በለወ አልተቀበሉም። የአስከፊና ፀያፍነቱን ያህል አምርረው ጠለተውታል፣ ተቃውመውታል። በመጨረሻም ብረት አንስተው ተዋግተውታል።

የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ህዝቦቾ መጀመሪያ ያካሄዱት ተቃውሞና ትግል ያልተደራጀ፣ ስትራቴጂና ታክቲክ የሌለው ግብታዊ፣ በአጥቢያ ባላባቶችና ሹመኞች ላይ ያነጣጠረ ነበረ። ይህ ተቃውሞና ትግል የተጫነባቸውን ጭቆና ከማላላት ይልቅ ሞት፣ እስራትና የአደባባይ ግርፋት ነበር ያተረፈላቸው። ይሁን እንጂ በዚህ ሞት፣ እስራትና የገበያ ላይ ግርፋት ውስጥ መልክ ያለው ትግል ተፀንሷል።

ዘውዳዊው ስርአት የዘረጋው ቢሮክራሲ የተማሩ ዜጎችን ሳያካትት ስርአቱን ጠብቆ ማቆየት ስላልቻለ፣ ቤሮክራሲውን በተማረ የሰው ሃይል መሙላትን ዓላማ ያደረጉ የትምህርት ተቋማት በትላልቅ የሃገሪቱ ከተሞች ተቋቋሙ። ይህ ለጥቂቶች ብቻ የመማር እድል የሰጠ ሁኔታ የገባር አርሶ አደር ብሄር፣ በሄረሰብና ህዝብ አባላት ለጆችን ተጠቃሚ አድርጓል ማለት ባይቻልም፣ በጣት የሚቆጠሩ ግን በአጋጣሚ የእድሉ ተጠቃሚ የሆኑበትን ሁኔታ ፈጥሯል።

እነዚህ ቢሮክራሲውን በሰው ሃይል ለማጨቅ ዓላማ የተቋቋሙ የትምህርተ ተቋማት በተለየ በ1950 ዎቹ የተመሰረተው የቀዳማዊ ኃ/ሰላሴ ዩኒቨረሲቲ፣ የስርአቱን ምንነትና በኢትዮጲያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦቸ ለይ የተጫነውን በሄራዊና ኢኮኖሚያዊ ጭቆና ምንጭና ባህሪ መረዳትና የስረአቱን ማንነት መተንተነ የሚችሉ ልሂቃንን አፈሩ። ከእነዚህ ልሂቃን

መሃከል ከመሳፈነቱና ከመኳንንቱ ወገን የሆኑ የስርአቱን አስቀያሚ ባህሪ በመረዳት ከገባር ልጆች ጋር ተሰልፈው ስርአቱን የተቃወሙም ነበሩበት። የተቃወሞው መሪ የሆኑም አሉ። እዚህ ላይ ዋለልኝን ያስታውሷል።

ከዚህ በኋላ በፊውዳላዊው ዘውዳዊ ስረአት ላይ የተቀሰቀሰው ተቃወሞ አየጎላ ሄደ። ትግሉ ግን ዋናውን የጭቆናውን ገፈት ቀማሽ የብሄር፣ ብሄረሰብና ሕዝብ ገባር አርሶ አደሮችን ያቀፈ ሳይሆን በከተማ አካባቢ የተገደበ፣ ልሂቃኑን እና ተማሪዎችን ያሳተፈ ነበር። ይህ የልሂቃንና የተማሪዎች ትግል ያልተደራጀ ቢሆንም የትግሉ ዓላማና የሚታገለውን አካል ማንነት ላይ ግነዛቤ ነበረው ማለተ ይቻላል።

ከተሞች አካባቢ ባልተደራጀ ሁኔታ የተቀጣጠለው የልሂቃንና የተማሪዎች ትግል በወቅቱ 90 በመቶ ገደማ ይሆን የነበረውን ገባር አረሶአደር ከገባር ጭሰኝነት ነፃ ማውጣተ ላይ ያተኮረ ነበር። በመሆኑም የትግሉ መሪ ሃሳብ መሬት ለነባር ባለቤቱ አርሶ አደረር "የመመለስ የመሬት ላራሹ" ጥያቄ ነበር።

በልሂቃን የሚመራው የተማሪዎች የተቃውሞ ንቅናቄ ከሌሎች ወቅታዊ ሁኔታዎች ከፈጠሯቸው የስርአቱ ቀወሶች ጋር ተዳመረው፣ በስራ አጥነት፣ በስራ ዋስትና እጦት፣ የመኖሪያ ቤት እጦት ሲነገላታ የኖረወ ጭቁን ከተሜ አሰለፎ ተቀጣጠለ፤ በተለይ በአዲሰ አበባ ትግሉ ስርአቱነ አሰጨንቆ ያዘው።

ይህ በጭቁን ከተሜዎቸ የታጀበ የገባር አርሶአደሩን ጥያቄ ያነገቡ ለሂቃንና ተማሪዎች ትግል በመጨረሻ ስርአቱን አንገዳገደው። ይህኔ ያንኑ ዘውዳዊ ስርአት ሲያገለግል የነበረው መለዮ ለባሽ ተነቃንቆ ሊፈርሰ የተሰነጣጠቀውን ስርአት ጠግኖ በአዲሰ መልክ የማስቀጠል ዓላማ ይዞ "ብሄራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ" በሚል ስያሜ ተደራጅቶ ብቅ አለ፤ በኋላ ወታደራዊ ደርግ የሆነወ ይህ ወታደራዊ ቡድን ነው። በመጨረሻም በተማሪዎች እና ጭቁን የከተማ ህዝብ ተገፍቶ ሰሩ የተነቀለውን ስርአት መውደቅ አብሰሮ የስልጣን ኮርቻ ላይ ጉብ አለ።

ወታደራዊ መኮንኖችንና የበታች ሹማምንትን የያዘው ይህ ወታደራዊ ቡድን (ወታደራዊ ደርግ) ግዚያዊ ወታደራዊ መንግስት መሰረተ። ስልጣን ላይ በወጣ በወራት ውስጥ ዘውዳዊ

ስረአቱን ጠግኖ በአዲስ መልክ የማስቀጠል ዓላማውን መተዉን በይፋ አወጆ ስልጣን ላይ ራሱን አደላደለ። ወታደራዊ ቡደኑ የንጉሰነገስቱን ፈላጭ ቆራጨነት በወታደራዊ ቡድን ፈላጭ ቆራጨነት የተካ ፈፁም አምባገነን ነበር።

ወታደራዊ ቡድኑ ስልጣን ላይ ራሱነ እንዳደላደለ ዘውዳዊውን ስርአት ለውድቀት ያበቃው እንቅስቃሴ መሪ ሃሳበ ለነበረው "መሬት ለአራሹ" ጥያቄ ምላሽ ሰጠ፣ የካቲት 1967 ላይ ባወጀው የገጠር መሬት ለአራሹ አዋጅ። የጭቁን ከተሜዎች ዋነኛ ችግር ለነበረው የስራ ዋስትና እጦትና የመኖሪያ ቤት አጦትም ምላሽ የሰጡ አዋጆችን አወጣ። እነዚህ አዋጆች ለአርሶ አደሩና ለከተማ ነዋሪው እፎይታ ፈጥረው ነበር። ይሁን እንጂ አርሶአደሩ በመሬቱ ያመረተው ምርት ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት እንዲኖረው አልተደረገም። በከተማወች አካባቢም የመኖሪያ ቤት እጥረትን በዘላቂነተ መፍታት አልቻለም፣ ስራ አጥነትንም አላቃለለም። በመሆኑም የርሶ አደሩም ሆነ የከተሜው ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ መሻሻል አለቻለም።

ወታደራዊው ደርግ ከሁሉም በላይ የዘውዳዊ ስርአተ ጭቆናዎች ሁሉ መሰረት ለነበረው ብሄራዊ ጨቆና ምላሽ መስጠተ አለፈለገም። የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ህዝቦች ለአንድ ክፍለ ዘመነ በቆዩበት ብሄራዊ ጨቆና እነዲቀጠሉ ተደረገ። ወታደራዊው ስረአት ሲያገለግለው እነደነበረው ዘውዳዊ ስርአት የወሰን አንድነት እነጂ የህዝብ አንድነት አላሳሰበውም። ለወታደራዊው ስረአት ኢትዮጵያ ማለት የተለያየ ማንነት ያላቸው ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዘቦች ሳይሆኑ ገኡዙ መሬት ነበር። በመሆኑም ለብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብትና ነፃነት መከበር ዋጋ ሳይሰጥ የወሰን አንድነትን ማስከበርን ዋነኛ ተግባሩ አደረገ።

በመሆኑም ለረጅም ግዜ ውስጥ ውስጡን ሲቀጣጠል የቆየውና ለንጉሰ ነገሰቱ ስረአት መፈረስ አየነተኛ ምክንያት የነበረው የብሄራዊ መብትና ነፃነት ጥያቄ ገንፈሎ ወጣ። በርካታ የብሄራዊ ነፃነት ግንባሮቸ ተደራጁ። ብረት አንስተው ዱር ገብተው በየአቅጣጫው ወታደራዊውን አምባገነን ስረአት የወጉት ጀመር። በወታደራዊ ደርግ ስረአት በትጥቅ ትግል ላይ የነበሩ በሄራዊ የነፃነተ ግንባሮች ሃያ ገደማ ነበሩ። በመጨረሻም ግንቦት 20፣

1983 ዓ/ም ወታደራዊውን ደርግ ዳግም ላይመለስ በሚችልበት አኳኋን አፈራርሰው አስወገዱት።

አሁንም በዘውዳዊውና በወታደራዊ የመንግስት ስርአቶች የነበረውን ብሄራዊ ጨቆናና ለብሄራዊ ነፃነት በየአቅጣጫው የተደረገውን ትግል መቀበል የሚጎመዘዛቸው ጠቂቶች አሉ። እነዚህ ወገኖች በሄራዊ የነፃነት ትግል የመጨረሻውን አሃዳዊ የመንግስት ስርአት - ወታደራዊ ደርግ ፈንቅሎ ዳግም ላይመለስ አስወግዶ የብሄሮች፣ በሄሮችና ሕዘቦች ብሄራዊና ኢኮኖሚያዊ ጭቆና የሌለባትን፣ የህዝቦች አንድነት ያላትን ፌደራላዊት ሃገረ ለመመስረት ሲነሱ እነዚህ ወገኖች "ሃገር ተቆረሰ፣ ተበታተነ . . ." የሚል ጩኸት አሰምተዋል። አሁንም ሰሚ አልቦ ጩከታቸው በዘጋው ጉሮሯቸው ያንኑ የድሮ ጩኸታቸውን እያንቋረሩ ይገኛሉ።

ከደርግ ውድቀት በኋላ የሰፈነው ዴሞክራሲያዊ ስርአት የአመለካከት ነፃነት በማስከበሩ የዘውዳዊና ወታደራዊ ስርአቶች ርዝራዦች አመለካከታቸውን በይፋ እያራመዱ ይገኛሉ። በአመለካከታቸው ተደራጅተው ለመንግስት ስልጣን እሰከመፎካከር የዘለቀ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የገኛሉ፤ ሞቶ የተቀበረው ፊውዳላዊ አመለካከታቸው የትም አላደረሳቸውም እንጂ።

ያም ሆነ ይህ ከደርግ ውድቀት በኋላ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ በኋላ ለአንድ መቶ ያህል አመታት በኢትዮጲያ ሰፈኖ የነበረው ለብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብትና ነፃነት እውቅና የነፈገ ጨቋኝ ስረአት ላይመለስ ተወግዶ በምትኩ ፍፁም አዲስ የመንግስት ስርአት ተገንብቷል፤ በኢፌዴሪ ሕገመንግስት።

**ይቀጥላል**